# ትግላችን

አለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር

ወርሃዊ መፅሄት

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የተዘጋጀ

## የ ዲ ሞ ክ ራ ሲ

## ጥ ያ ቄ

የመፅሄት አዘጋጅ ቦርድ፣
P.O.BOX 3198
103 64 STOCKHOLM 3
SWEDEN

ቁጥር 2

ሰኔ 1968

# ይዘት


—ስለ አዲሱ ዲሞክራሲ .................... 1

—ዲሞክራሲ ለምን ለማን .................... 10

—የዲሞክራሲ መብት ይዘትና አጠቃቀም በልዩ
ልዩ ሥርዓተ ማኅበሮች .................... 17

—ስለሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ አምባገነንነት ...... 21

—ብሔረሰቦች የገዛ ዕድላቸውን መወሰን ስለአላቸው
መብት ........................... 24

—ሶሻሊዝም ስለብሔረሰቦች መብት ያለው አቋም ... 30

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር

The Ethiopian Students' Union
in Europe

ውድ ጓዶች ጓዲቶች

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር ስለኢትዮጵያ ጊዜያዊ ሁኔታ ሰፊ ጥናት ለማድረግ እአአ ከነሐሴ 8 እስከ 15 1976 በምዕራብ በርሊን ከተማ 16ኛው ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባኤውን ያካሄዳል:: በዚህ ጉባኤ ላይ ከ15 ሃገሮች በላይ የሚመጡ የቅርንጫፍ ማህበራት አባላት ይገኛሉ:: ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የጉባኤው ተካፋዮች ከምስራቅ አውሮፓ በመሆናቸው የምዕራብ ገንዘብ/ከረንሲ/ ለማግኘት ስለማይችሉ፣ ማህበራችን ለጉባኤው ዝግጅት፣ ማካሄጃ ወዘተ ሰፊ እርዳታ ያስፈልገዋል:: ማህበራችን ባለፈው 11 ዓመታት ውስጥ ያካሄደውን ፀረ ፊውዳልና ፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግል፣ በአሁኑ ወቅትና ወደፊትም የሚያካሄደውን ተጋድሎ የደገፉ የሚደግፉ አብዮታዊ ድርጅቶች ቡድኖች ግለሰቦች ወዘተ የእርዳታ እጃቸውን እንዲዘረጉለት አብዮታዊ ጥሪ ያደርጋል::
ማህበራችን ከእራሱ በመርህ ላይ ከተመሰረተ የአብዮታዊያን የትግል አጋዶች በስተቀር ሌላ የሚተማመንበት ሃይልም ሆነ የገንዘብ ምንጭ የለውም:: አይሻምም:: ከነአበሩው ወገን የወጣ ድርጅት/ፌዴሬሽን የሚል የውም አንዱ መሠረታዊ ነገር ይኸው ነው::

ከአብዮታዊ ሰላምታ ጋር

THE ETHIOPIAN STUDENTS' UNION IN EUROPE

የሚከተለውን የባንክ አካውንት ለመጠቀም ይቻላል:—
Tesfaye/ Mesfin (ESUE), Berliner Bank, Konto Nr. 9946080700